# - 14 -

## ስኬታማ ጋብቻ: የተበላሸው ትስስር

<u>ማስታወሻ:-</u> ይህ መጣጣፍ በባለትዳሮች መካከል መከባበር መስፈን እንዳለበት የሚጠቁም ነው። መከባበር ስንል በየትኛውም ሁኔታ ውስጥ አካላዊ፣ ስሜታዊም ሆነ ስነ ልቦናዊ ጥቃትን መራቅን ያጠቃልላል። በራስም ሆነ በቤተሰብ ላይ የሚደረግን የጥቃት ሁኔታ መቀበል ትዕግስት ነው ሊባል አይችልም። ባይሆን ግልጽ ጥቃት ነው፤ በደል ነው። አላህ (ሱ.ወ) በደልን አይቀበልም፣ እኛም እንዲሁ ልንቀበል አይገባም። በባልና ሚስት መካከል አላህ ውዴታንና እዝነትን አስፍኗል።

አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ይላል:-

﴿ وَمِنْ ءَايَٰتِهِۦٓ أَنْ خَلَقَ لَكُم مِّنْ أَنفُسِكُمْ أَزْوَٰجًا لِّتَسْكُنُوٓا۟ إِلَيْهَا وَجَعَلَ بَيْنَكُم مَّوَدَّةً وَرَحْمَةً ۚ إِنَّ فِى ذَٰلِكَ لَءَايَٰتٍ لِّقَوْمٍ يَتَفَكَّرُونَ ﴾

**“ለናንተም፣ ከነፍሶቻችሁ ሚስቶችን፣ በነርሱ ትረኩ ዘንድ መፍጠሩ፤ በመካከላችሁም፣ ፍቅርንና እዝነትን ማድረጉ ከአስደናቂ ምልክቶቹ ነው። በዚህ ውስጥ ለሚያስተውሉ ሕዝቦች ተዓምራት አልሱ።”** (አር-ሩም : 21)

ይህንን አንቀጽ በበርካታ የጋብቻ ሥነ ሥርዓቶች ላይ በተደጋጋሚ አንብበናል ወይም ሰምተናል። ግና ስንቶቻችን ነን መልዕክቱን ያስተዋልነው? ምን ያህሎቻችን ነን ትዳር አላህ (ሱ.ወ.) በዚህ አንቀጽ ውስጥ በገለፀው መልኩ በፍቅር እና በእዝነት መሆን እንዳለበት የገባን? የብዙዎቻችን ጋብቻ በፍቺ ሲጠናቀቅ ምክንያቱ ምን ነበር? እነኚህ ሁሉ ልንጠይቃቸው የሚገቡ ጥያቄዎች ናቸው።

እንደ የLove and Respect መጽሐፍ ደራሲ ዶክተር ኤመርሰን ኤ. አባባል የስኬታማ ጋብቻ ሚስጥር መልሱ ቀላል ነው። ዶክተሩ ከረጅም ጊዜ ጥናቱ በኋላ እንደደረሰበት ድምዳሜ ከሆነ የወንዱ ዋንኛ ፍላጎት ነው ብሎ ያስቀመጠው ነገር “መከበር” ሲሆን የሴቷ ዋነኛ ትኩረት እና ፍላጎት ደግሞ “ፍቅር” እንደሆነ ነው። ዶክተሩ እንደሚሉት “ኢ-ጤናማ ግንኙነት” ብለው የሰየሙት የትዳር ሕይወት ምክንያቱ ሚስት ለባሏ ክብር ሳይኖራት ስትቀር እና ባል ለሚስቱ ፍቅርን ሲነፍግ ነው። ዶ/ሩ ሁለቱም ተጣማሪዎች በመካከላቸው ያለን አለመግባባት በማጋጋል ተገቢ ላልሆነ ችግር እንዴት እንደሚጋለጡ አብራርተዋል። አንዲት ሚስት ባለቤቴ አይወደኝም ብላ ማሰብ ከጀመረች ዘወትር ምላሿን የምታሳየው እሱን ባለማክበርና በመናቅ ነው። በዚህም የተነሳ ባል ደግሞ በተራው የባሰ እልህ ውስጥ የሚገባበት ሁኔታ ይኖራል።

የዚህ መፍትሄው ደግሞ- ዶክተሩ እንደሚያስቀምጡት ሚስት ለባሏ ያለምንም መስፈርትና ቅድመ-ሁኔታ አክብሮት እንዲኖራት ሲሆን፤ ባል ደግሞ በበኩሉ ለሚስቱ እሱም ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ፍቅር ማሳየት እንዳለበት ነው። ይህም ማለት ሚስት ለባሏ እንዳከብረው ከፈለገ በመጀመሪያ እሱ ሊወደኝ ይገባል ማለት እንደሌለባት ነው። እንዲህ የምትል ከሆነ ከባሏ በኩል የባሰ ጥላቻን እንጂ ፍቅርን የምታገኝ አትሆንም። ባልም በበኩሉ እንድወዳት ከፈለገች ሚስቴ መጀመርያ ልታከብረኝ ይገባል ማለት የለበትም። እንዲህ የሚል እና የሚያደርግ ከሆነ ከሚስቱ የሚተርፈው ነገር ቢኖር ንቀት ብቻ ነው።

ሁለቱ እንዳቸው ለአንዳቸው የሚያሳዩት ፍቅር በሆነ መስፈርት የታሠረና የተገደበ መሆን የለበትም። ያለምንም መስፈርት መዋደድ፣ ያለምንም ቅድመ ሁኔታ መከባበር ይኖርባቸዋል።

ስለመከባበር ፅንሰ ሀሳብ ስናወራ መነሻችንን ቁርኣንና ነቢያዊ ሐዲሥን መሠረት አድርገን ነው። ከትዳር ግንኙነት ጋር በተያያዘ ሁለት ሊተኮርባቸው የሚገቡ ዋና ዋና ጉዳዮች አሉ። የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) ለወንዶች ባስተላለፉት መልዕክት እንዲህ ብለዋል :-

"ለሴቶች መልካም ዋሉ፤ እነርሱ ከጎድን አጥንት ነው የተፈጠሩት፣ ከሁሉም ጎባጣ የሆነው ክፍል ደግሞ በላይ በኩል ያለው ነው። ለማቃናት ብትሞክር ትሰብረዋለህ፤ ከተውከው ደግሞ እንደጎበጠ ይቀራል፣ ስለሆነም ለሴቶች መልካም ሁኑ።" ብለዋል። (ቡኻሪና ሙስሊም እንደዘገቡት)

እንዲሁም ስለ ሴቶች ጉዳይ የበለጠ አፅንኦት ሲሠጡ እንዲህ ብለዋል :- "በኢማን ጉዳይ እጅግ ምርጡ አማኝ ምርጥ ሥነምግባር ያለው ነው። ከናንተ መካከል ምርጡ ሰው ማለት ለሚስቱ ምርጥ የሆነው ነው።" (ቲርሚዚ እንደዘገቡት)

የአላህ መልዕክተኛ(ሰ.ዐ.ወ.) እንዲህም ብለዋል:-

"አማኝ ወንድ አማኝ ሴትን ሙሉ በሙሉ አይጥላ። ከባህሪዋ አንዱን ካልወደደ በሌላኛው መልካም ባህሪዋ ሊደሰት ይገባል።" (ሙስሊም እንደዘገቡት)

አላህ (ሱ.ወ.) በቁርአኑ እንዲህ ብሏል:-

﴿وَعَاشِرُوهُنَّ بِٱلْمَعْرُوفِ ۚ فَإِن كَرِهْتُمُوهُنَّ فَعَسَىٰٓ أَن تَكْرَهُوا۟ شَيْـًٔا وَيَجْعَلَ ٱللَّهُ فِيهِ خَيْرًا كَثِيرًا﴾

**«በመልካም ተኗኗሩዋቸው። ብትጠሉዋቸውም (ታገሱ)። አንዳችን ነገር ብትጠሉ አላህም በእርሱ ብዙ ደግ ነገርን ሊያደርግ ይችላልና።»** (አን-ኒሳእ : 19)

በነዚህ ታላላቅ ወርቃማ መልዕክቶች ወንዶች ለሚሰቶቻቸው መልካምና አፍቃሪ እንዲሆኑ ታዘዋል። እንዲሁም በነርሱ ላይ መጥፎ ባህሪን በተመለከቱ ጊዜ ስህተቶቻቸውን በእዝነትና በፍቅር እንዲያልፉ ተመክረዋል።

በሌላ በኩል ኢስላም ሴቶችን ሲያዝ ደግሞ ትኩረቱ ይለያል። ሴቶች ለምንድን ነው ለባሎቻቸው መልካምና አፍቃሪ እንዲሆኑ በተደጋጋሚ ያልታዘዙት? ምናልባት ያለምንም ቅድመ ሁኔታ መውደድ የሴት ልጅ ተፈጥሯዊ ሁኔታ ስለሆነ ሊሆን ይችላል። ጥቂት ወንዶች ብቻ ናቸው ሚስቶቻቸው እንደማይወዷቸው ሲናገሩ የሚደመጡት። ሚስቶቻቸው እንደማያከብሯቸው የሚናገሩት ግን ብዙ ናቸው። ከሚስቶች አንፃር በቁርአንና በሐዲሥ ትልቅ አፅንዖት የተሰጠውም ይህ ጉዳይ ነው። ማክበር።

ማክበር ስንል በተለያዩ መንገዶች ሊገለጽ ይችላል። ክብርን ለማሳያ እጅግ ወሳኝ ከሆኑ መንገዶች መካከል አንዱ የአንድን ሰው ፍላጎት ማክበር ነው። አንድ ሰው "ምክርህን አከብራለሁ" ያለ እንደሆነ "ምክርህን ለመተግበር ዝግጁ ነኝ።" ማለቱ ነው። መሪን ማክበር ማለት መሪዎች የሚያዙትን መፈፀም ማለት ነው። ወላጆችን ማክበር ማለት ከፈቃዳቸውና ከትዕዛዛቸው አለመውጣት ማለት ነው። ባልን ማክበር ስንልም ፍላጎቱን ማክበር ማለት ነው።

የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) እንዲህ ብለዋል "አንዲት ሴት አምስት ወቅት ሰላትዋን ከሰገደች፣ ወሯን (ረመዷንን) ከፆመች፣ ብልቷንም ከጠበቀችና ባለቤቷን ከታዘዘች በፈለግሽው በር ጀነት ግቢ ትባላለች።" (ቲርሚዚ እንደዘገቡት)

እኛ ሴቶች ባሎቻችንን እንድናከብርና ፍላጎቶቻቸውን እንድንፈጽም የታዘዝነው። ለምንድነው? ልንል እንችላለን። ምክንያቱም ወንዶች ተጨማሪ ኃላፊነት ስለተሠጣቸው ነው። አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ይላል፡-

﴿ ٱلرِّجَالُ قَوَّٰمُونَ عَلَى ٱلنِّسَآءِ بِمَا فَضَّلَ ٱللَّهُ بَعۡضَهُمۡ عَلَىٰ بَعۡضٖ وَبِمَآ أَنفَقُواْ مِنۡ أَمۡوَٰلِهِمۡۚ ﴾

**«ወንዶች በሴቶች ላይ ቂሚዎች (አሳዳሪዎች) ናቸው። አላህ ከፊላቸውን በከፊሉ ላይ በማብለጡና (ወንዶች) ከገንዘቦቻቸው (ለሴቶች) በመስጠታቸው ነው።»** (አን-ኒሳእ : 34)

አንድ ባል መከበር አለበት ሲባል ቅድመ ሁኔታና መስፈርት ተቀምጦለት መሆን የለበትም። ባል በማክበር የታዘዘውም ሴቶች ደካማና ከወንዶች በታች ስለሆኑ አይደለም። የማክበር መንፈሱ የጭቆና መንፈስን ያዘለ አይደለም። ወንዶች ሴቶችን እንዲጎዱ ዕድል የሚያመቻችም አይደለም። በዚያ መልኩ ሊታየንም አይገባም። ቁርአን፣ ነቢያዊ አስተምህሮም ሆነ የተለያዩ ጥናቶች እንደሚያመለክቱት ይበልጥ ባሏን አክባሪ

የሆነች ሴት ከወንዱ በኩል ከፍ ያለ ፍቅርና መልካምነት እንደሚጠብቃት ነው። በናቀችው ቁጥር ደግሞ የሚጠብቃት መልስ ጭካኔና የአጋሯን እዝነት ማጣት ነው።

አንድ ሰው ለማታከብረው ሚስቱ ጭምር ለምን መልካም እና አፍቃሪ መሆን እንዳለበት ራሱን ሊጠይቅ ይችላል። ለዚህ መልስ የሚሆነን አንድ የውመር ኢብኑል ኸጧብ ታሪክ ስላለ እሱን ማየቱ ይጠቅማል። ውመር የሙስሊሞች ኸሊፋ እያሉ አንድ ሰው ከሚስቱ በኩል የሚደርስበትን በደል ብሦቱን ለመናገር ወደርሣቸው ሄደ። በራቸው ላይ ሲደርስ ግን ሚስታቸው ስትጮህባቸው ሰማ። በሁኔታው ተገርሞ ለመመለስ ሲያስብ ውመር አይተውት ኖሮ ጠሩት። ሰውዬውም የመጣበትን ጉዳይ ነገራቸው። በሚስቱ እንደተማረረ። ግና የውመርን ሁኔታ ሲያይ ነበር ጉዳዩን ላለመናገር አስቦ ሊመለስ የነበረው። በታላቁ ኸሊፋ በውመር ኢብኑል ኸጧብ የተጮኸ ሚስቱ በሱ ላይ ብትጮህ ምኑ ይገርማል! ውመር ግን ለሰውዬው ሚስታቸው ብዙ እንደቻለቻቸው ነገሩት። ልብሴን ታጥብልኛለች፣ የቤቴን ንጽህና ትጠብቃለች፣ ምቾት እንዲሠማኝ ትጨነቅልኛለች፣ ልጆቼን ትንከባከብልኛለች - እያሉ ዘረዘሩለት። እሷ ለኔ ብላ ይህን ሁሉ የምታደርግ ከሆነ ድምጿን ከፍ ብታደርግብኝ እንዴት አልችላትም? አሉት።

ታሪኩ ለሁላችንም የሚያስተላልፈው ትልቅ መልዕክት አለ። ለወንዶች ብቻ አይደለም ትምህርቱ። የመቻቻልና የትዕግስት ድንቅ መገለጫ ነው። ለስኬታማ ትዳርም ወሳኙ ነገሮች ሁለቱ ናቸው። ከዚህም ባለፈ በመጨረሻው ዓለም ለትዕግስተኞች የተዘጋጀውን ሽልማት ማሰብ ያስፈልጋል።

አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ይላል፡-

﴿إِنَّمَا يُوَفَّى ٱلصَّٰبِرُونَ أَجۡرَهُم بِغَيۡرِ حِسَابٖ﴾

«ታጋሾቹ ምንዳቸውን የሚሰጡት ያለግምት ነው።» (አዝ-ዙመር : 10)